# አባይ የውስጥ ትኩሳት ማብረጃ...

ይለቃል ስንሻው 01/18/14

ኢትዮጵያ የምትከተለው የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መሰረት የሚያደረገው የአገሪቱን ኤኮኖሚያዊ ጠቀሜታና አገራዊ ህልውናን በማረጋገጥ እንዲሁም በማንኛውም አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ባለመግባትና ለህዝቦች ጥቅም በጋራ በመስራት ላይ ነው። ይህ ኤኮኖሚክ ዲፕሎማሲን መሰረት ያደረገው የአገራችን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ባለፈው አስርት ዓመታት አገሪቱን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት እንድታስመዘግብ በማስቻሉ አገራችን ከራሷ አልፋ ጎረቤት አገሮችን መጥቀም እንደቻለች አንዳንድ አብነቶችን ማንሳት ይቻላል።

ኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርዓትን መተግበር ከጀመረች ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ፈጣንና ተከታታይነት ያለው ኤኮኖሚያዊ እድገት በማስመዝገቧ ህዝባችን ብቻ ሳይሆን ጎረቤት አገሮች ህዝቦችም ጭምር አገራችን ካስመዘገበችው የኤኮኖሚ እድገት በቀጥታ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

ከቅርብ አመታት ወዲህ አገራችን ለሁሉም ጎረቤት አገራት ዜጎች እንደሁለተኛ አገር በመቆጠር ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ አገራት ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ስደተኞችን ማስጠለል ብቻ ሰይሆን ለስደተኞች ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር በተባባሩት መንግስታት ድርጅት የስደተኞች ኮሚሽን ሙገሳን ተችሯታል። ይህ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያችን ትክክለኝነት አንዱ ማሳያ ተደርጎ ሊታይ የሚችል ውጤት ነው።

በሌላ በኩል የአገራችን ኤኮኖሚ በፈጣን ሁኔታ ማደግ ሲጀምር ከጎረቤት አገራት ጋር በንግድ፣ በባህል፣ በሰላም ማስከበር፣ ወዘተ ትስስሩ እየጠነከረ መምጣት ጀምሯል። ኢትዮጵያና ጅቡቲ እጅግ የጠነከረ ግንኙነት በመፍጠር ዛሬ ላይ አንዱ አገር ለሌላኛዋ

የህልወና ምንጭ እስከመሆን መድረሳቸውን መመልከት ይቻላል። ጅቡቲ የባህር በሯን ለኢትዮጵያ በማከራየት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ስታገኝ፣ በተመሳሳይ ኢትዮጵያ የተለያዩ የግብርና ውጤቶችን ለጅቡቲ በማቅረብ ተመሳሳይ ጥቅም ማግኘት ችላለች።

ከዚህ ባሻገር ኢትዮጵያ የተለያዩ የመሰረተ ልማት አውታሮችን ዘመናዊ የመንገድ ግንባታ፣ የባቡር ማስመር ዝርጋታ፣ በአየር በረራ መስመሮች ማስፋፋት፣ የሃይል አቅርቦት ወዘተ በማካሄድ የሁለቱን አገራት ህዝቦች ግንኙነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲደርስ አድርጋለች። በተመሳሳይ ኢትዮጵያ ከሌሎች ጎረቤት አገሮች ማለትም ከደቡብ ሱደን፣ ሱዳን፣ ኬንያ እንዲሁም ሶማሊያ ጋር አካባቢውን በኤኮኖሚ ሊያስተሳስሩ የሚችሉና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን ሊያጠናክሩ የሚችሉ የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን የመንግድ ፣ የሃይል አቅርቦት፣ የአካባቢ ሰላም፣ ንግድ ወዘተን እንዲስፋፉ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ነች።

ኤርትራ ህዝብም ቢሆን ኢትዮጵያ ካስመዘገበችው የኤኮኖሚ እድገት ተጠቃሚ መሆን የቻለበት ሁኔታዎች እንዳሉ ማየት ይቻላል። አምባገነኑ የኤርትራ መንግስት በህዝቡ ላይ በሚያደርሰው ከፍተኛ በደል ሳቢያ በሺዎች የሚቆጠሩ ኤርትራዊያን ስደተኞች ወደ አገራችን ተሰደዋል። አገራችን እነዚህን የኤርትራ ስደተኞች አቅም በፈቀደ ሁሉ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን ለምሳሌ፣ የትምህርት እድልን በተመለከተ እስከ ሁለተኛ ዲግሪ ድረስ እንዲማሩ በመፍቀድ አጋርነቷን አሳይታለች።

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ መልካም ነገሮች የመነጩት አገራችን ከምትከተለው የውጭ ፖሊሲ መሆኑን መገንዘብ የሚያዳግት አይመስለኝም። በተመሳሳይ አትዮጵያ ታላቁን የህዳሴ ግድብ መሰረት ስትጥል አገሪቱ ያለባትን ከፍተኛ የሃይ አቅርቦት እጥረት ለመፍታት እንዲቻል እንዲሁም በተመጣጣኝ ክፍያ ለጎረቤት አገሮች ሃይል በማቅረብ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ የምታገኝበትን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ነው።

ኢትዮጵያ ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች በአለም አቀፍ ስምምነት መሰረት የሚተዳደሩ መሆናቸውን ከግንዛቤ በማስገባት የህዳሴው ግድብን ለሃይል ልማት እንጂ ለመስኖ እንዳልሆነ በተደጋጋሚ አሳውቃለች። በመሰረቱ ኢትዮጵያ እንደሱዳን ሰፊ የመስኖ መሬት

የሌላት ከመሆኑም በላይ የግድቡ ስፍራ ወደ ሱዳን ጠረፍ የተጠጋ በመሆኑ የህዳሴው ግድብ ለመስኖ ስራ የሚያገለግል አይደለም። ይህን ጉዳይ ኢትዮጵያ ባለስልጣናት ለሚመለከታቸው አካላት በተደጋጋሚ አሳውቀዋል።

ግብጽና ሱዳን ይታላቁ የኢትዮጵያን ታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት የ1929 እና 1959 ዓ.ም የቅኝ ግዛት ስምምነቶችን የሚጥስ በመሆኑ እንደማይቀበሉት ሲወተውቱ የቆዩ ቢሆንም፤ ሱዳን የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነትና የልማት ፖሊሲዎች መርምራ በመረዳቷ እንዲሁም ከዚህ ቀደም ከተጠናቀቁት ፕሮጀክቶች ያገኘችውን ጥቅም በማስላት አቋሟን በማስተካከል ለህዳሴውን የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ድጋፏን እንደምትሰጥ አሳውቃለች። ሱዳን ከኢትዮጵያ ፕሮጀክቶች በተለይ ከተከዜ የሃይል ማመንጫ ግድብ ከፍተኛ ጥቅም ማግኘት በመቻሏ የኢትዮጵያ የልማት ስራዎች አካባቢውን ሊጠቅሙ የሚችሉና የቀጠናውን የኢኮኖሚ ትስስሩን የሚያሳድጉ መሆናቸውን ስትመለከት ለታላቁን የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክትም ድጋፉን በተገኘው መደረክ ሁሉ አረጋግጣለች።

የኢትዮጵያ መንግስት ህዳሴው ግድብ ፕሮጀክት ይፋ ባደረገበት ውቅት እነደገለጸው አገሪቱ የጀመረችውን ፈጣን የኤኮኖሚ እድገት ለማስቀጠል የሚቻለው እየታየ ያለውን ከፍተኛ የሃይል አቅርቦት ችግር መቅረፍ ሲቻል መሆኑን ተገንዝቧል። የአገራችን ኤኮኖሚ ከግብርና ወደ ኢንደስትሪ በሚያደርገው የመዋቅር ለውጥ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የሃይል አቅርቦትን እንደሚያስፈልግ ቅቡል ሃቅ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስት አካባቢን የማይበክሉ ትላልቅ የውሃ ሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶችን ለመገነባት በመወሰን እንደ ጊቤ ሶስትና ታላቁ የህዳሴ ግድብ ያለ ግዙፍ የሃይል ማመንጫዎችን መገንባት ጀመረ።

አገራችን ከነዚህ ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሚመነጨውን ሃይል አቅርቦት ፍላጎቷን ካሟላች ብኋላ ለጎረቤት አገራት በተመጣጣኝ ዋጋ የሃይል ምንጭ በመሆን የቀጠናውን ኤኮኖሚያዊ ትስስር ለማሳደግ ጠንክራ እየሰራች ትገኛለች። ከዚህም ባሻገር አገራችን ለጎረቤት አገራት በተመጣጣኝ ዋጋ ከምታቀርበው የሃይል አቅርቦት የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ይስችላታል። እንግዲህ 6 ሺህ ሜጋ ዋት ሃይል የሚያመነጨው ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ሲጠናቀቅ ግብፅና ሱዳን በተመጣጣኝ ዋጋ የሃይል አቅርቦት

ከማግኘታቸው ባሻገር  የህዳሴው ግድብ የወንዙን ስነምህዳራዊ ሁኔታ  መጠበቅ ስለሚችል በየወቅቱ  የሚዋዥቀውን የወንዙን የወሃ መጠን በማስተካከል  አመቱን ሙሉ የተመጣጠነ ፍሰት እንዲኖረው ያደርጋል።

ኢትዮጵያ ቀድማ ይዛ  የተነሳችው አቋም ሁሉም የአባይ ተፋሰስ አገራት ከወንዙ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ፕሮጀክት ለመገንባት  እንጂ፣ ኢትዮጵያ ግብፅን ወይም ሱዳንን ወይም ሌላ አገርን ለመጉዳት አስባ እንዳልሆነ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

ሰሞኑን የአባይ ጉዳይ እንደ አዲስ በተለያዩ ሚዲያዎች ላይ የትኩረት መስክ ሆኖ ሰንብቷል። ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብፅ በፈረንጆቹ አዲስ አመት መጀመሪያ ማለትም ጥር 04 እስከ 05  በካርቱም ያደረጉትን ውይይት የግብፅ ተደራዳሪዎች ይዘውት በቀረቡት አጓጉል አጀንዳዎች ውይይቱ  ፈር ሳይዝ እንዲበተን ሆኗል።

አንዳንድ  የግብፅ  ፖለቲከኞችና ምሁራን ስለ ህዳሴው ግድብ በቂ መረጃ ሳይኖራቸው ቀርቶ ወይም  ሆኔታውን ሆን ብለው  አንጋደው ለህዝባቸውና ለአለም ማህበረሰብ በማቅረብ ያለባቸውን  የፖለቲካ ትኩሳት  በአባይ ጉዳይ  ለመሸፋፈን  ያሰቡ ይመስላል። ኢትዮጵያ የህዳሴውን ግድብ በተመለከተ ለተፋሰሱ አገራትም ሆነ  ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ በቂ መረጃዎችን አቅርባለች።  ግብጽን ጨምሮ ከተለያዩ አገራት የተውጣጡ ቴክኒክ ኮሚቴ እንዲዋቀር ተደርጎ የህዳሴው ግድብ በአካባቢው አገራት ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ እንዲገመግም ፈቅዳለች። ይህ በሆነበት ሁኔታ አንዳንድ የግብጽ ፖለቲከኞችና ምሁራን ስለህዳሴው ግድብ እንዲህ ያለ እርስ በርሱ የሚጋጭ መገለጫዎችን በየሚዲያው የሚሰጡት  በቂ መረጃ ሳይኖራቸው  ነው ብሎ ማሰብ  የዋህነት ይመስለኛል።

አንዳንድ ግብፃዊያን ፖለቲከኞችና ሙሁራን የውስጥ ችግሮቻቸውን በአባይ ጉዳይ ለማድበስበስ ሲሉ  የላይኞቹ የአባይ ተፋሰስ አገራት በተለይ ኢትዮጵያ በግብፅ ላይ ጫና እያደረገች እንደሆነ በማስመሰል ሊጨበጥ የማይችል ታሪክ ሲያወሩ ይታያሉ። በእርግጥ

ኢንቴቤው ስምምነት  የተፋሰሱ አገራት መካከል  ፍተሃዊ የውሃ አጠቃቀም የሚያሰፍን ከመሆኑም በላይ በቀጣይ የቀኝ ግዥ ስምምነቶች ተቀባይነታቸው ያበቃበት የትብብር ማአቀፍ ነው።

አንዳንድ ግብጻዊያን  ምሁራን የተጣመመ የአገራቸውን መንግስት ሃሳብ ደግፈው መከራከራቸውን ስመለከትና የእኛ አገር አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎችና ምሁራኖች የአገራችንን ጥቅም ለማስጠበቅ  የሚከተሉትን  አቋም ጋር ሳነጻጽረው  የእኛዎቹ አቋም አሳፋሪ  ሆኖብኛል። አገር መውደድ ማለት ምን ማለት ነው?  አንዳንድ የግብጽ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና ምሁራን  የ86 በመቶ የሆነው የአባይ ውሃ ምንጭ የሆነችውን አገራችንን ጠብታ ውሃ መጠቀም የለባትም የሚል መከራከሪያ ሃሳብ ይዘው ሳሉ የእኛም አገር  አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችና ምሁራንም ይህን የግብጽ አቋም  የሚደግፍ የሚመስል ሃሳብ ሲያንሸራሽሩ ይስተዋላሉ።

ግብፃዊያን ፖለቲከኞችና ምሁራን  አገራችን ይጠቅማታል የሚሉትን  ፍትሃዊ ያልሆነ ምክንያት  አንግበው  የአገራቸውን  ጥቅም ለማሰጠበቅ   ሲሯሯጡ፤  አንዳንድ የእኛ አገር የተቃዋሚ ፓርቲ  አመራሮች ደግሞ እውነታን በመካድ ለመናኛ የፖለቲካ ትርፍ ሲሉ የጥፋታቸው ተባባሪ በመሆን  እብረዋቸው ሲያጫፍሩ  ይስተዋላሉ። ለማንኛውም ይህን ጉዳይ ለዛሬ ልለፈውና በሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ።

የኢትዮጵያ መንግስት ፍትሃዊና እውነታ ላይ የተመሰረቶ፣ አለም አቀፍ መርሆዎችን መሰረት አድረጎ እየተንቀሳቀሰ ባለበት ሁኔታ በፖለቲካ አመለካከት ከመንግስት ጋር ተለያይተናል   በሚል የአገርን ጥቅም አሳልፎ መስጠት ማስተዛዘብ ብቻ ሳይሆን የሚያጠያይቅም ጉዳይ ነው። ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተመሳሳይ አይዲዮሎጂ ወይም የፖለቲካ አተያይ ሊኖረው ባይችልም በአገራችን ዘለቄታዊ ጥቅም ላይ ግን ከቶ ልንለያይ አይገባንም።

*ግብጻዊያን  አሰዋን  ግድብ  ከውሃ  ማጠራቀሚያነቱ  ባሻገር ተጨማሪ ትርጉም እንደሚሰጡት ሁሉ፣ የታላቁ  ህዳሴው ግድብም  ለእኛ ኢትዮጵያዊያኖች ከኤኮኖሚያዊ ጠቀመሜታው  ባሻገር የሚያስተላልፈው  ምልዕክት እንዳለ መታወቅ አለበት።  የአሰዋን*

***ግድብ ለግብጻዊያን የብሄራዊ ኩራታችሁና የአንድነታችሁ መገለጫ እንዲሆን በየሚዲያው እንደምትገልጹት ሁሉ ታላቁ የህዳሴ ግድብም ለእኛ ኢትዮጵያዊያን ተመሳሳይ ትርጉም ያለው በመሆኑ በማንኛውም ረገድ ፕሮጀክቱ እውን እንዲሆን ከመንግስታችን ጎን እንደምንሰለፍ ግብጻዊያን ፖለቲከኞችና ምሁራኖች ልትገነዘቡት ይገባል።***

ኢትዮጵያ ለዘመናት ትታወቅበት ከነበረችው ድህነትና ጦርነት አባዜ ተላቃ በራሷ ገቢ እንዲህ ያለ ባለ ብዙ ቢሊዮን ዶላር ፕሮጀክት መገንባት መጀመሯ በራሱ ትልቅ ድል ነው። የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር አቶ መለስ ዜናዊ የታላቁን የህዳሴ ግድባችንን መሰረት በጣሉበት ጊዜ እንዳሉት “**መሃንዲሶቹም እኛው፣ የገንዘብ ምንጮቹም እኛው፣ ግንበኞቹም እኛው** በማለት የተናገሩት ፕሮጀክቱ ለኢትዮጵያዊያን የተለየ ትርጉም የሚሰጥ መሆኑን ለማሳየትም ጭምር ነበር።

የኢትዮጵያ መንግስት ይህን ባለብዙ ቢሊዮን ዶላር ፕሮጀክት እቅድ ሲነድፍ የፋይናንስ ምንጭ እንደሚሆነው የተማመነው የህዝብ ድጋፍንና የውስጥ ገቢን እንጂ ከውጭ የሚገኝ ብድርንም ሆነ ስጦታን እንዳልሆነ ፕሮጀክቱ በተበሰረበተ ወቅት ቃል በቃል ተነግሯል።

ግብጻዊያን ኢትዮጵያ ከአባይ ውሃ የመጠቀም መብት እንዳላት የአለም አቀፍ የውሃ ስምምነቶች እንደሚፈቅድላት ቢያውቁም አንዳንድ የግብጽ ፖለቲከኞችና ምሁራን ሆን ብለው ነገሮችን በማጣመም ኢትዮጵያ ከወንዙ የመጠቀም መብት እንደሌላት በማስመሰል ለህዝባቸው ሲነግሩት ይስተዋላሉ።

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የውሃና ግድብ ባለሙያ የሆኑት ዶ/ር አህመድ አልሃናዊ በቅርቡ ለአልወፍድ ድረ-ገፅ እንደተናገሩት በአባይ ውሃ ኢትዮጵያ ተጠቃሚ የመሆን መብት እንደሌላት ለማብራራት ሲሉ የተለያዩ ተጨባጭነት የሌላቸውን ነገሮች ሲተነትኑ ነበር። ከዶክተሩ ትንታኔ ውስጥ ለአብነት ያልኳቸውን እንደሚከተለው አነሳቸዋለሁ። ዶክተሩ የታላቁን ህዳሴ ግድብ የሚገነባበት ስፍራ የመሬት መንቀጥቀጥ የሚያጠቃው

በመሆኑ ለሱዳንና ግብፅ ትልቅ ስጋት ነው የሚል ትችት ሰንዝረዋል። ዶ/ር አህመድ አልሃናዊ የትኛውን ጥናት ተመርኩዘው ይህን እንዳሉ ግን አልጠቆሙም።

ዶ/ር አህመድ አልሃናዊ ያልተገነዘቡት ነገር እንደው ኢትዮጵያ ይህን ያህል መጠን ያለው (ቢሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር) ፕሮጀክት ያለ በቂ የከርሰ ምድር ጥናት ለመስራት የምትነሳ ተላላ አገር ትምስላቸው ይሆን? በአካባቢው የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የህዳሴው ግድብ የሚሰራበት አካባቢ እስካሁን በመሬት መንቀጥቀጥ ተመትቶ እንደማያውቅ እኚህ ምሁር አጥተውት ሳይሆን የህዳሴውን ግድብ በተመለከተ በታችኛው የተፋሰሱ አገራት ህዝቦች ዘንድ ብዥታ ለመፍጠር ታስቦበት የተደረገ አካሄድ ነው።

እንደ ዶ/ር አህመድ አልሃናዊ ትንታኔ ኢትዮጵያ ከአባይ መጠቀም የምትችለው በግብፅ ይሁንታ ላይ ተመስርታ ብቻ እንደሆነ ሊነግሩን ይፈልጋሉ። ኢትዮጵያ በአባይ ላይ ግድብ ለመስራት ሃሳብ ያነሳችው በመጀመሪያ በጋማል አብዱልናስር ከዚያም በአንዋር ሳዳት፣ ቀጥላም በሙባረክ ጊዜ ሙከራ እንዳደረገች ይገልፁና በሙርሲ ዘመን መገንባት መጀመሯን ሊነግሩን ይፈልጋሉ።

ይሁንና ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ የልማት ስራዎችን እስካሁን ሳታከናውን የቆየችበት ምክንያት በውስጥ ችግሯ ተተብትባ እንጂ ዛሬ አንዳንድ የግብጽ ፖለቲከኞችና ምሁራኖች ሊነግሩን እንደሚሞክሩት ኢትዮጵያ የቅኝ ገዥ ስምምነቶችን ተገዥ ሆና አይደለም። ኢትዮጵያ ከአባይ የውሃ ድርሻ የመጠቀም መብት እንዳላት ብታውቅም በራስ አቅም እንዲህ ያሉ የብዙ የቢሊዮን ዶላር ወጪን የሚጠይቁ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን ማልማት ይቅርና ትንንሽ የሃይል ማመንጫዎችን መገንባት ተስኗት ህዝቦቿ ለዘመናት በኩራዝ ጢስ ሲጠበሱ ኖረዋል።

ዶ/ር አህመድ አልሃናዊ ትንታኔቸውን በመቀጠል እስራኤል የአባይን ውሃ በሲናይ አሻግረን እንድንሰጣት ግብጽን በተደጋጋሚ ብትጠይቅም አልሳካ ስላላት በላይኞቹ የተፋሰሱ አገራት በኩል እጇን አስገባች ይሉናል። ይህ የዶ/ር አህመድ አልሃናዊ አባባል

አስገራሚ ጉዳይ ነው። ዶክተሩ የህዳሴውን ግድብ ጉዳይ ከእስራኤል ጋር ለማገናኘት የሚደርጉት መሯሯጥ የማይመስልና እጅግ ደካማ መረጃ እንደሆነ ማየት እቻላል። ግብፅና እስራኤል መካከል ችግር ካለባቸው በዚያው በመስመራቸው መፍትሄ መፈለግ ተመራጭ ይሆናል እንጂ፣ ከህዳሴው ግድብ ጋር የእስራኤልን ጉዳይ ማገናኘት ተገቢ አይመስለኝም።

ኢስራኤል ከአንዳቸውም የራስጌ የአባይ ተፋሰስ አገራት ጋር ድንበር የማትጋራ አገር በመሆኗ በቀጥታ የአባይ ውሃ ተጠቃሚ ልትሆን አትችልም። እንግዲህ እውነታው ይህ ሆኖ ሳላ አንዳንድ የግብጽ ምሁራንና ፖለቲከኞች እንደምን ብለው ሁኔታዎችን በማሳሳብ ነገሩን ፖለቲካዊ ሽፋን እንዲኖረው ለማድረግ ሲሯሯጡ ማየት አስገራሚ ጉዳይ ነው።

በአገራዊ ጉዳይና በብሄራዊ ጥቅማቸው ግብፃዊያን አንድ ናቸው። እንግዲህ እኛ ኢትዮጵያዊያን ከግብጻዊያን ልንማራቸው የሚገቡን እንዳንድ ነገሮች እንዳሉ ማየት ይቻላል። እስካሁን ባለው ሁኔታ አንዳንድ የግብጽ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ምሁራን ከመንግስታቸው ጎን በመሰለፍ የግብፅን ጥቅም ያስጠብቃሉ የሚሉትን ነገር ሲያራምዱ አይተናል። በእኛ ሀገር ግን አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎችና ምሁራኖች በአገራዊ ጉዳይና በብሄራዊ ጥቅማችን የሚነካ ነገሮችን በተመለከተ እንኳን የሚሄዱበት መንገድ እጅግ አስገራሚ ብቻ ሳይሆን አሳፋሪም ጭምር ነው።

መንግስታት ይመጣሉ ይሄዳሉ፤ ስርዓትም ይለወጣል፤ ነገር ግን አገርና ህዝብ ግን ቋሚ ናቸው፤ በእኛ አገር እነዚህን ነገሮች ለይቶ ለዘለቄታ ጥቅም ሲባል የሚደረግ እንቅስቃሴ አይታይም፤ ሁሉንም በማጇመል፣ በዳበሳና በማጥላላት የፖለቲካ በሽታ ተዘፍቀናል። በሁሉም ነገረ ከመንግስት አቋም በተቃራኒው መሰለፍ የሚቀናቸው የእኛ አገር አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎችና ምሁራን የህዳሴው ግድብ ግንባታን ኢህአዴግ ለፖለቲካ ፍጆታ ብሎ የጀመረውና ከዳር ሊያደርሰው አስቦ እንዳልሆነ በማስመሰል ህብረተሰቡ ለፕሮጀክቱ የሚያደርገውን ድጋፍ እንዲጠራጠር የሚያደርጉ ትችቶችን በመሰንዘር በቀጥታ ከአንዳንድ ግብጻዊያን ፖለቲከኞችና ምሁራን ጋር ያበሩ አስመስሎባቸዋል።

ዶ/ር አህመድ አልሃናዊ እንደሚሉት ኢትዮጵያ የህዳሴውን ግድብ በተመለከተ ብድርና እርዳታ እንዳታገኝ በማድረግ ግብጽ ጫና መፍጠር ትችላለች ብለዋል። የዶ/ር አህመድ አልሃናዊ ንግግር መረዳት የሚቻለው ኢትዮጵያ በአባይ ላይ የልማት ስራዎችን እንዳትሰራ ለማድረግ ግብጽ ለዘመናት የተለያዩ ቴክኒኮችን ትጠቀም እንደነበር አማላካች ነው። ከላይ ለማንሳት እንደሞከርኩት ግብጻዊያን ያልተረዱት ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ ታላቁን የህዳሴ ግድብ ለመገንባት ሲነሱ ከየትኛውም አገር ሆነ ድርጅት ብድርም ሆነ እርዳታ እናገኛለን የሚል እቅድም ሆነ ተስፋ እንደሌላቸው ግብጻዊው ዶ/ር ሊያውቁት ይገባል።

ዶክተሩ ትንታኔቸውን በመቀጠል እንዲህ ይሉናል "እኛ ግብፃዊያን ኢትዮጵያዊያኖች እንዳይጎዱ ለማድረግ ስንል የመሬት መንቀጥቀጥ በማያጠቃው የጥቁር አባይ ኮረብታማና ጠንካራ አለት ያለባቸውን አካባቢዎች በመምረጥ በርካታ ትናንሽ ግድቦችን በመስራት የህዳሴው ግድብ ከሚያመነጨው አስር እጥፍ የኤሌክትሪክ ሃይል እንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል" ብለዋል። ይህ የዶክተር አህመድ አልሃናዊ ንግግር የአንድን ሉአላዊ አገር ክብር በእጅጉ የሚነካ ነው። እኛ ኢትዮጵያዊያን የራሳችን ብሄራዊ ኩራት የተላበስን ማንም እንደፈለገ የማይዘውረን መሆናችንን ከአደዋ ታሪክ የተማሩ አይመስለኝም። በየትኛውም መልኩ የግብጽ ፖለቲከኞችና ምሁራን የምንሰራውንና የማንሰራውን ፣ የሚሆነንንና የማይሆነንን እንዲነግሩን አንፈልግም።

በቅርቡ የግብፅ፣ ሱዳንና የኢትዮጵያ ተወካዮች በካርቱም ባደረጉት ውይይት ላይ የግብጽ ተደራዳሪዎች ኢትዮጵያ **"የመተማመኛ ማጎልበቻ መርህ"** የሚል ሃሳ እንድትቀበል ለማግባባት ሲጥሩ ነበር። ግብፅ ያቀረበችው "የመተማመኛ ማጎልበቻ መርህ" በ1959 ስምምነት ግብጽና ሱዳን በእንግሊዝ ሞግዚትነት ያደረጉትን የአባይን ወሃ ክፍፍል ስምምነት መሰረት ከ84 ቢሊዮን ኪዮቢክ ሜትር አመታዊ የወንዙ ፍሰት ውስጥ ግብጽ የተቸራትን የ55.5 ቢሊዮን ኪዮቢክ ሜትር ድርሻዋን ኢትዮጵያ እንድታጸድቅላት የሚጠይቅ ነው።

በእርግጥ ኢትዮጵያ በታላቁ የህዳሴው ግድብ ፕሮጀክት ለሃይል ማመንጨነት እንጂ ለመስኖ ልማት ስለማያገለግል በወንዙ የውሃ መጠን እንደማይቀንስ በተደጋጋሚ የገለጸች ቢሆንም፤ የግብጽ ፖለቲከኞች "ሌባ እናት ልጇን አታምንም" እንደሚባለው "የመተማመኛ ማጎልበቻ መርህ" የሚል ጉዳይን የመደራደሪያ ነጥብ አድርጎ ማቅረብን በኢትዮጵያዊያን ተደራዳሪዎች ተቀባይነት እንደማይኖረው አጥተውተ አይመስለኝም።

አንዳንድ ግብጻዊያን ፖለቲከኞችና ተደራዳሪዎች የውስጥ ችግራቸውን በአባይ ጉዳይ ለመጀቦን እንዲያመቻቸው እንዲህ ያሉ ተልካሻ ምክንያቶችን በማንሳት ድርድሩን ያለውጤት እንዲበተን አድርገዋል። የግብጻዊያን ተደራዳሪዎች ያነሱት ሌላው ጉዳይ የላይኛው የተፋሰሱ አገራት ማንኛውንም ፕሮጀክት መስራት በሚፈልጉ ወቅት በቅድሚያ ለግብፅ በማሳወቅ ፍቃድ መጠየቅ እንደሚገባቸው የሚያደርግ አካሄድን ነው። በርግጥ በጋራ ሃብት ላይ መነጋገርና መመካከር ተገቢ አካሄድ ቢሆንም፣ ግብጽን ፍቃድ ሰጪና ነሺ አድርጎ ማቅረብ ግን ተገቢ አካሄድ አይመስለኝም።

አል ሻርቅ አልአወሰጥ ከተባለው የግብጽ ድረ-ገፅ የመስኖ ሚኒስትር የሆኑት ዶክተር አብዱል ሙጠሊብን ጠቅሶ እንደዘገበው የኢትዮጵያ መንግስት ግድቡን ለመስራት የገንዘብ ችግር ያለበት በመሆኑ የግድቡን 30 በመቶ አጠናቅቄአለሁ የሚለው ለፖለቲካ ፍጆታ እንጂ ግድቡ በታቀደለት መንገድ እየተከናወነ አይደለም ብለዋል።

ሚንስትሩ ያልተረዱት አንድ ነገር ያለ ይመስለኛል። የኢትዮጵያ መንግስት ለፖለቲካ ፍጆታ ብሎ የሚያከናውነው ከህዝብ የተደበቀ አንዳች ነገር እንደሌለ ሊያውቁት ይገባል። ግብጻዊያን ፖለቲከኞች ስለህዳሴው ግድብ አፈጻጸም ለእኛ ኢትዮጵያዊያን ሊነግሩን ከቶ አይቻላቸውም። አንዳንድ የግብጽ ፖለቲከኞችና ምሁራን ሊረዱት የሚገባው ነገር የህዳሴው ግድብ የህዝብ ፕሮጀክት በመሆኑ የየእለት እንቅስቃሴው ለህብረተሰቡ እንደሚገለፅ ሊያውቁት ይገባል።

አንዳንድ የግብፅ ምሁራንና ተቃዋሚዎች የመንግስታቸውን የተንጋደደ ሃሳብ በተለያየ ጌጣጌጥ በማስዋብ ህዝባቸውንና አለምን ለማሳመን ሲሯሯጡ በተቃራኒው የእኛ አገር አንዳንድ ምሁራንና ተቃዋሚዎች የት ጋ ይሆኑ? እውነት የእኛ አገር አንዳንድ

ምሁራንና ተቃዋሚዎች ምን እየሰሩ እንደሆነ ተገንዝበውትስ ይሆን? የአገር ፍቅር ምን ማለት እንደሆንስ ገብቶአቸው ይሆን? ስል ራሴን ጠየቅሁ። እነሱ አመድ ጨብጠው ዱቄት እንደሆነ ምለው ተገዝተው ሲናገሩን፤ እኛ ግን ዱቄት ይዘን ዱቄት እንደሆነ በአንድ አፍ መናገር ተስኖናል።

አንዳንድ በሰላማዊ መንገድ እንታገላለን የሚሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎችና ጽንፈኛው የዳያስፖራ ፖለቲከኞች ከግብጻዊያን ፖለቲከኞችና ምሁራን ባልተናነሰ መልኩ በየአደባባዩ የታላቁን ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ሲያብጠለጥሉት ይደመጣሉ። በተመሳሳይ መርዶ አብሳሪ የሆኑት ኢሳትና የተቃዋሚ ፓርቲ ድረ-ገጾች ሰሚ ጆሮ አጡ እንጂ ህብረተሰቡ ለህዳሴው ግድብ የሚያደርገውን ድጋፍ እንዲያቆም ሲወተውቱ ይስተዋላሉ።

የመስኖ ሚኒስትሩ ዶክተር አብዱል ሙጠሊብ ግብፅ በልጆቿ፣ በታሪኳና በባህሏ ጠንካራ አገር በመሆኗ በግድቡ ምክንያት የሚፈጠረውን አሉታዊ ነገሮችን ለመከላከል ወደ ፈልግነው ቦታ ብንሄድ በርካታ መረጃዎችና ሰነዶች የአሉን በማለት አገራቸው የአባይ ብቸኛ ባለቤት እንደሆነች አድርገው ይናገራሉ። ግብፅ ማንንም ለምና አታውቅም፣ ወደፊትም አትለምንም፣ መብቷን የምታስከብርበት በቂ አቅም እንዳላትም ሚንስትሩ በማስፈራራት ጭምር ሊነግሩን ይፈልጋሉ።

በቅድሚያ የኢትዮጵያ መንግስት አገራችን ተጠቅማ ሌሎችንም ሊጠቅም የሚችል ፕሮጀክቶችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረጉ ሊያስመሰግነን እንጂ ሊያስወነጅለው የሚገባ ጉዳይ መሆን የለበትም። ግብጻዊያን አንዲት ጠብታ ውሃ ለአባይ ሳያበረክቱ ለዘመናት ወንዙን በብቸኝነት መጠቀማቸው ሳያንሳቸው፤ የወንዙ አድራጊ ፈጣሪ መሆን ዳድቷቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ የወንዙን 86 በመቶ ውሃ የምታበረክት አገር መንግስት፣ እንዲህ ያለ አካባቢውን በጥቅም ሊያስተሳስር የሚችል ፕሮጀክት ተግባራዊ ለማደረግ እየሰራ መሆኑ እጅግ የሚገርም ታላቅነት ነው። በዚህ በሳል የመንግስታችን አካሄድ በየትኛውም ፍርድ ቤት ማንንም መርታት ስልምንችል በመንግስታችን አርቆ አሳቢነት ልንኮራ ይገባል። ኢትዮጵያ በታሪኳ በውጭ ሃይሎች ተንበርክካም፤ እንዲሁም በውጭ አገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብታም አታውቅ።

እንግዲህ ሱዳናዊያን፣ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ከገነባቻቸው  የልማት ስራዎች በተለይ የውሃ ሃይል ልማትን በተመለከተ ተጠቃሚ መሆናቸውን በተግባር በመረዳታቸው ቀድመው ይዘውት የነበረውን አቋማቸውን ሙሉ በሙሉ በመቀየር  ኢትዮጵያ ለምትገነባው የህዳሴ ግድብ ሙሉ ድጋፋቸውን  ቸረዋል። በተመሳሳይ  አንዳንድ የግብጽ ፖለቲከኞችና ምሁራን  የአባይን ጉዳይን ለውስጥ ትኩሳታቸው ማብረጃነት ከመጠቀም ተቆጥበው የሱዳንን ፈለግ በመከተል  ለአካባቢው መልማት ድጋፋቸውን የሚሰጡበት ወቅት ሩቅ እንደማይሆን ተስፋ እናደርጋለን።

ቸር እንሰንብት!